# ምርጫው የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያን ብቻ ነው

ክፍል አንድ

ለሚ ዋቄ 11-27-14

5ኛው ዙር ሃገራዊ ምርጫ ከስድስት ወራት ያነሰ ግዜ ቀርቶታል። የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫው የግዜ ሰሌዳ መሰረት ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ እየቀረቡ የምርጫ ምልክታቸውን አሳውቀው እየወሰዱ የገኛሉ። በዘንድሮው ምርጫ ላይ 75 ፓርቲዎች ናቸው የሚፎካከሩት። ከእነዚህ መሃከል 52ቱ በክልል ደረጃ የሚወዳደሩ ሲሆኑ የተቀሩት 23ቱ በፌደራል ወይም በሃገር አቀፍ ደረጃ  የሚወዳደሩ ናቸው። በምርጫው ላይ የሙወዳደሩት ሁሉም ፓርቲዎች እነደየአፈጣጠርና ባህርያቸው የምርጫ ዝግጅት እያደረጉ ነው።

በሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ብቻ የሚያምኑና ምርጫን ብቸኛው የህዝብ የስልጣን ውክልና ማግኛ መንገድ አድርገው የሚወስዱት ለዚህ ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ እየተዘጋጁ ነው። ሲመች ሕገወጥነትን፣ ካልተመቸ ደግሞ ህጋዊነትን እያጣቀሱ የሚንቀሳቀሱትም እዚህና እዚያ እየረገጡ ነው። በአንድ ወገን “በምርጫው ላይ እንሳተፋለን፣ ሕዝቡ ዴሞክራሲያዊ መብቱን እንዲጠቀም እናደርጋለን” ሲሉ በሌላ በኩል ደግሞ የተቃውሞ ህዝባዊ እንቅስቀሴ ለማድረግ መዘጋጀታቸውን እያወጁ ነው።

የመንግስት የስልጣን ምንጭና ብቸኛ ባለቤት የሆነው ሕዝብም የፖለቲካ ፓርቲዎችን እንቅስቃሴ እየታዘበ ምን አዲስ ነገር ይዘውለት እነደሚቀርቡ እየተጠባበቀ ነው። በሃገሪቱ የሚካሄዱትን ምርጫዎች በበላይነት የሚመራውና ምርጫዎች ነፃ፣ ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ አኳኋን እንዲካሄዱ የማደረግ ሃላፊነት በህገመንግስት የተሰጠው ብሄራዊ ምርጫ ቦርድም የምርጫውን ሂደት የግዜ ሰሌዳ አዘጋጅቶ ምርጫውን እየመራ ነው። ለምርጫው አስፈላጊውን  ዝግጅት ማጠናቀቁን አሳውቋል።

ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ተቃዋሚዎች በየአካባቢወ ጽህፈት ቤት  መከፈት፣ ከምርጫው ጋር የተያያዙ ስብሰባዎችን ማድረግና የመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ የሚያጋጥማቸውን ችግሮች ተቀበሎ ለመፍታት መዘጋጀቱን አስታውቋል። በአጠቃላይ በምርጫው ላይ አጋጠመን

የሚሉት ፕሮግራሞች ላይ ከፓርቲዎች ጋር ለመወያየት እቅድ ይዟል። ይህን በምርጫው ላይ ለሚፎካከሩ ፓርቲዎች አሳወቋል። እርግጥ ከምርጫ ይልቅ ረብሻን ተስፋ ያደረጉ ጥቂት ፓርቲዎቸ “ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ያቀረብናቸው ጥያቄዎች ላይ ለመወያየት ፍቃደኛ አይደለም” ብለው ውዝግብር መፍጠሩን ተያይዘውታል።

እንግዲህ የምርጫ ዋነኛ ባለድርሻ የሆኑት ሕዝቡ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ እንቅስቃሴ ውስጥ ገብተዋል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ ጉዳይ የማይመለከተው፣ የምርጫ ባለድርሻ ያለሆነው የምርጫ ጉዳይ በሩቁ እንኳን የማይመለከተው የአውሮፓ ህብረት እና/ወይም የህብረቱ አባል የሆኑ የምእራባውያን ሃገራት ዲፕሎማቶችም መራወጥ ጀምረዋል። የአውሮፓ ህብረት የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያን ብቻ የሆነው ምርጫ ላይ “በያገባኛል” ባይነት መቅነዝነዙ ብዙዎችን አሰገርሟል፤ አብሽቋልም።

የአውሮፓ ህብረት አባል ሃገራት ዲፕሎማቶች  የምርጫውን ሂደትና የፓርቲዎችን እንቅስቃሴ በተመለከተ በየክልሉ እየተዘዋወሩ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችን እያነጋገሩ መሆኑን ሰመተናል። በየክልሉ “ተቃዋሚዎች ቢሮ ለመከፈትና ለመነቀሳቀስ የሚያጋጥማቸው ችግር፣ የህግ አከባበርና የሰበአዊ መብት አጠባበቅ ጉዳዮችን እየተከታተሉ ነው” መባሉን ሰምተናል።

የአውሮፓ ህብረት ይህን እነዲያከናውን አልተጋበዘም። ህብረቱ በመጪው ምርጫ ላይ በታዛቢነት ስለመሳተፉ እስካሁን በይፋ የተነገረ ነገረ የለም። ህብረቱ በምርጫ ታዛቢነት የሚሳተፈው በመንግስት ከተጋበዘ ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ ምርጫውን ለመታዘብ የሚገኝበት አግባብ የለም።

የአውሮፓ ህብረት እስካሁን ባለው ሁኔታ መጪውን ምርጫ ይታዘብ አይታዘብ በይፋ የሚታወቅ ነገር ባይኖርም፣ “ህብረቱ በሆነ መነገድ ወደስልጣን ልነመጣ የሚያስችለ ሁኔታ ሊያመቻች ይችላል” የሚል ተስፋ ያደረባቸውና ህብረቱ በታዛቢነት አለመሳተፉ እንደ

ችግር እንዲታይ የሚፈልጉ ወገኖች “በታዛቢነት አይሳተፍም” አያሉ ከወዲሁ አያወጁ ይገኛሉ።

እርግጥ ነው የአውሮፓ ህብረት በምርጫ ታዛቢነት ሊጋበዝ የማይችል መሆኑ ድንጋጤ የፈጠረባቸው አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች መኖራቸው የታወቃል። እንደውም ምርጫው ላይ ላለመሳተፍ የውጭ ታዛቢን ጉዳይ እንደቅድመ ሁኔታ የማስቀመጥ አዝማሚያም ያሳዩም አሉ። የኢትዮጵያ ህዝብ ግን የአውሮፓ ህብረት በምርጫ ታዛቢነት እነዲሳተፍ መጋበዙ ወይም አለመጋበዙ የሚያመጣው ምንም ተፅእኖ እንደሌለ ያውቃል። ከአስራ ሁለት ሚሊየን በላይ ኢትዮጵያውያንን የሚወክሉ ሃገር በቀል ሲቪል ማህበራት እንዲሁም የህዝብ ምርጫ ታዛቢዎች የአፍሪካ ህብረትን የመሳሰሉ ዓለም አቀፍ ተቋማት ታዛቢ ቡድን በመላ ሃገሪቱ የምርጫ ጣቢያዎች በመገኘት ምርጫውን እንደሚታዘቡም ያውቃል።

እውነቱን ለመናገረ የኢትዮጵያ ህዝብ የአውሮፓ ህብረት በምርጫ ታዛቢነት መጋበዙ እነጂ አለመጋበዙ አያስገርመውም። በመሆኑም “የአውሮፓ ህብረት በዘንድሮው ምርጫ በታዛቢነት አይሳተፍም” ለሚለው ወሬ ምንም ዋጋ አልሰጠውም። አብዛኛው ሰላማዊ ዜጋ እንደውም “የአውሮፓ ህብረት ምርጫውን እንዲታዘብ አለመጋበዙ ተገቢ ነው” የሚል እመነት ነው ያለው።

የአወሮፓ ህብረት በምርጫ ታዛቢነት አለመጋበዝን “ተገቢ ነው” ያሰኘው፣ የህብረቱ የምርጫ ታዛቢ ቡድን ከዚህ ቀደም በተካሄዱ ምርጫዎች ላይ ያሳየው ከታዛቢነት ስነምግባር ያፈነገጠ ፀያፍ ድርጊት ነው። የአውሮፓ ህብረት በተለየ በ1997 እና በ2002 ዓ/ም የተካሄዱትን 3ኛና 4ኛ ዙር ምርጫዎች በታዘበበት ግዜ የምርጫውን ሂደትና የምርጫውን ክንውን በገለልተኝነት ታዝቦ ይህን ከመመስከር ይልቅ፣ በምርጫው ውጤት ላይ አስቀደሞ አቋም ይዞ ውጤቱ ከዚህ ቅድመ ውሳኔው ጋር ባለመጣጣሙ ምርጫውን ወደማብጠልጠለ ተሻገሮ እንደነበረ ይታወሳል።

በ1997 ዓ/ም የተካሄደው 3ኛው ዙር ሃገራዊ ምርጫ ላይ የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን ምርጫውን ተከትሎ ያወጣው ወቅቱን ያልጠበቀ ሪፖርት ታዛቢ ቡድኑ በምርጫው ውጤት ላይ አሰቀድሞ ይዞት የነበረው አቋም የተንፀባረቀበት ፍፁም ገለልተኝነት

የጎደለውና ተጨባጭነት የሌለው ነበር። ይህ ገለልተኝነት የጎደለውና ተጨባጭ ያልሆነ የአውሮፓ ህብረት ሪፖርት ምርጫውን ተከትሎ የቀድሞው ቅንጅት ህገመንግስታዊውን ስርአት በሃይል ለመናድና ከህዝብ ውክልና ውጭ ስልጣን ለመቀማት ላደረገው ሙከራ አስተዋፅኦ ነበረው። የአወሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን ምርጫ 97ን ተከተሎ ያወጣው ሪፖርት ላይ ከዚህ ቀደም ብዙ ስለተባለ በድጋሚ ማንሳቱን አስፈላጊ አይደለም።

ይሁን እንጂ ምርጫ 97 ላይ የተገኘው የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን ምን ያህል ገለልተኝነት የራቀው እነደነበረ ለማስታወስ የታዛቢ ቡደኑ መሪ የነበሩት አና ጎሜዝ ስልጣን የመመንተፉ እቅድ ነዳፊ ከነበሩት ዶ/ር ነገደ ጎበዜ ጋር ያላቸውን ትስስር ለመግለፅ ብዙዎች ሃና ጎበዜ የሏቸዋል የያዙትንና አስካሁን በተለያየ አጋጣሚ የሚያንፀባርቁትን የተወሰኑ አቋሞች እንመልከት።

የአወሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን መሪ የነበሩት አና ጎሜዝ ምርጫውን ተከተሎ የተቀሰቀሰውን ህገመንግስታዊ ስርአት የመናድ አቋም ያራምዱ በነበሩ ወገኖች እንደጀግና ታይተው እንደነበረ እናስታውሳለን። አና ጎሜዝን ከአቴጌ ጣይቱ ጋር ለማነፃፃረ የዳዳቸውም ነበሩ፤ በተለይ “ህገመንግስታዊው ስርአት በሃይል መናድ አለበት” የሚል ፅንፍ የረገጠ አቋም የያዙ በውጭ ሃገራት በሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ዘንድ። እነዚህ ፅንፍ የረገጡ “ህገመንግስታዊ ስረአቱ በሃይል መናድ አለበት” የሚል የህዝብ ንቀት የሚንፀባረቅበት አቋም ይዘው ለዚህ ዓላማ ገንዘብ እያዋጡ የሚልኩ ወገኖች በሚያዘጋጇቸው ፕሮግራሞቸ ላይ አና ጎሜዘ ካልተገኙ አይሆንላቸውም ነበር። እንዲያውም በ1998 ዓ/ም በአሜሪካ ተዘጋጅቶ የነበረ አንድ ፕሮግራም ላይ በቀረበ የመቀሰቀሻ ዘፈን “ ኢትዮጵያ እናታችን፣ አና ጎሜዝ እህታችን” ተብሎ ተዚሞ እንደነበረ ይታወሳል። በምን መስፈርት እንደሆነ ባይታወቅም አና ጎሜዝ የሃገርን ያህል ስብእና ተሰጥቷቸው ነበር።

ይህ ሁሉ የሆነው አና ጎሜዝ ህገመንግስታዊ ስረአቱን በሃይል ለመናድ በዶ/ር ነገደ ጎበዜ የተነደፈው ፕሮግራም ይፈፀመ ዘንድ በምርጫ ታዛቢነተ ሽፋን ሁኔታዎችን በማመቻቸት ላደረጉት አስተዋፅኦ ውዳሴ ለማቅረብ ነው። ውዳሴው ሲትየዋ በቀጣይነትም ከአውሮፓ ህብረት፣ ከህብረቱ አባል መንግስታትና ሌሎች በምእራባውያን የሚደገፉ የሰብአዊ መብት

ተሚጋቸ ነን ባይ ቡደኖች ጋር በመተባበር ህገመንግስታዊ ስርአቱን የመናድ ተልእኳቸውን እንዲያገዟቸው ለማነሳሳትም ነው።

ይህ ሁኔታ ፅንፍ የረገጡት ተቃዋሚዎች ምእራባውያን በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እንዲገቡ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን አሳይቷል። ፅንፈኛ ተቃዋሚዎቹ እነርሱ ስልጣን ማግኘት ከቻሉ ኢትዮጵያ  በባእድ ተፅእኖ ስር መውደቋ ምንም የማያሳስባቸው ባንዳ የባንዳ ልጆች ናቸው። ታዲያ በዚህ የፅንፈኛ ተቃዋሚዎች ሙገሳና ውዳሴ ራሳቸውን ኢትዮጵያን እነደፈለጉ የመዘወር አቅም ያላቸው አድርገው የወሰዱት አና ጎሜዝ፣ በተለያየ አጋጣሚ አቋማቸውን ገልፀዋል። በዚህም በህዝብ ውክልና ስልጣን የተረከበው ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ላይ የመረረ መሰረተ ቢስ ጥላቻ እንዳላቸው በይፋ አሳውቀዋል።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢዴፓ)ን ወክለው የቀደሞው ፓርላማ አባል የነበሩት አብዱራህማን አህመዲን “ስለ አና ጎሜዝ እኔም የምለው አለ” በሚል ርዕስ ባለፈወ ዓመት ታህሳስ ወር ላይ በአይጋ ድረ ገፅ ባስነበቡት ፅሁፍ አና ጎሜዝን የተመለከቱ እውነታዎችን አጋርተውናል። የአና ጎሜዝን ማንነት በግልፅ ስለሚያሳዩ ልጠቅሳቸው ወደኳለሁ።

አቶ አብዱራህህማን የኢትዮጵያን ፓርላማ በመወከል የአፈሪካ፣ የካረቢያንና የፓሰፊከ (አፓካ) ፓርላማ እና የአውሮፓ ፓርላማ የጋራ ጉባኤ የልኡካን ቡድን  አባል በመሆን ባገለገለባቸው አመታት ከአና ጎሜዝ ጋር በተደጋጋሚ መገናኘታቸውን አውስተው፣ በእነዚህ አጋጣሚዎች ስለሴትየዋ የተገነዘቧቸውን እውነታዎች ነው ያጋሩን። አቶ አብዱራህማን ከአና ጎሜዘ ጋር በአካል ተገናኝተው በተጫወቱበተ አንድ አጋጣሚ በገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ላይ ያላቸውን ጥላቻ እንደገለፁላቸው አሰታውሰዋል። “እነዚህን ሰዎች (ኢሀአዴጎችን) አውቃቸዋለሁ። ፈላጭ ቆራጭ አምባገነኖቸ ናቸው። የዛሬ ሰላሳ ዓመት የእኔም ፓርቲ እነዲህ ነበር . . . ሰዎችን ይገድል ነበር . . .” ብለዋቸው እንደነበረ ያስታውሳሉ፤ አቶ አብዱራህማን።

ልብ በሉ፤ አና ጎሜዝ  የፖርቱጋል ሶሻሊስት ፓርቲ አባል ናቸው። ታዲያ ይህ እርሳቸው አባል የሆኑበት የሃገራቸው ፓርቲ ከ30 ዓመታት በፊት አምባገነን የነበረ ሊሆን ይችላል። ፓርቲያቸውን በዚህ ድረጊቱ ሊያዝኑበት፣ ሊወቅሱት ይችላሉ፤ ይህ የአና ጎሜዝና

የፖርቹጋላዊያን ጉዳይ ነው። ከዚህ ፓርቲ ጋር በግዜም በታሪክም አንዳችም የሚያገናኘው ነገር የሌለውን ኢ.ህአዴግ ከሚጠሉት ከሰላሳ ዓመታት በፊት ከነበረው የሃገራቸው ፓርቲ ጋር ተመሳስሎብኛል ባይ ናቸው። በምን ተመሳሰለባቸው? አይታወቅም።

ይህ ሴትየዋ በኢ.ህአዴግ ላይ ያደረባቸው ጥላቻ ምንም ተጨባጭ ምክንያት የሌለው፣ መሰረተ ቢሰ ጥላቻ (prejudice) መሆኑነ በግልፅ ያሳያል። አና ጎሜዝ ሲመሩት የነበረው የምርጫ 97 ታዛቢ ቡድን ሪፖርትም ከዚህ ጥላቻ የመነጨ ነበር። ኢ.ህአዴግን ስለሚጠሉ እንዲያሸንፍ አይፈልጉም ነበር፤ በህዝብ ድምፅ ማሸነፉን ሲያወቁ ይህን እውነት ጎመዘዛቸው። “ጉዳዩ የኢ.ትዮጵያውያን ነው” ብለው መተውም አልሆን አላቸው። እናም ሁከት ሊያስነሳ የሚችል ሪፖርት ቸከቸኩ፤ የሂው ነው ታሪኩ።

አና ጎሜዝ መሰረተ ቢስ ጥላቻቸው በህገወጥ መንገድ ህገመንግስታዊ ስርአቱን ለመናድ ከሚንቀሳቀሱና ምናልባትም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአሸባሪነት ከተፈረጁ ቡድኖች ጋር ጭምር አወዳጅቷቸዋል፤ ሴትየዋ የእነዚህ ቡድኖች ዓላማ አጋዥ ሆነው ተሰልፈዋል። የቀደሞው ፓርላማ አባል የነበሩተ አቶ አብዱራህማን በፅሁፋቸው ለዚህ ማስረጃ ሰጥተውናል፤ ተጨባጭ ማስረጃ። በአቶ እብዱራህማን ፅሁፍ ላይ የቀረበው ማስረጃ እንዳለ እጠቅሰዋለሁ።

*“ከወ/ሮ አና ጎሜዝ ጋር በተያያዘ በስፔን ሀገር ያጋጠመኝ ሁኔታ እስከ አሁን ድረስ ይገርመኛል፡፡ እኔ ከተሳተፍኩባቸው የአፍሪካ፣ የካሪቢያንና የፓስፊክ (አካፓ) ፓርላማ እና የአውሮፓ ፓርላማ የጋራ ጉባዔዎች አንዱ በስፔን የተካሄደው ነው፡፡ ስፔን ስብሰባውን ያዘጋጀቺው በዋና ከተማዋ ማድሪድ ሳይሆን፤ በደቡባዊ ስፔን ወደ አፍሪካ አህጉር ጠጋ ብላ፣ ካናሪ ደሴቶች አጠገብ በምትገኝ “ተነሪፌ” በተባለች የስፔን ግዛት በሆነች ትንሽ ደሴት ነበር፡፡ ተነሪፌ 800ሺህ ሕዝብ የሚኖርባት የቱሪስት መናኸሪያ ደሴት ናት፡፡*

*በስብሰባው ሂደት በአንዱ ቀን ወደ ስብሰባው አዳራሽ ስገባ ለስብሰባው ተሳታፊዎች የሚሰራጩ ወረቀቶች በሚደረደሩበት ጠረጴዛ ላይ፤ አናቱ ላይ የኢ.ትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በደማቁ የታተመበት ወረቀት ዓይኔን ሳበው፡፡ አንዱን ቅጂ አነሰሁና እዚያው ቆሜ አነበብኩ፡፡ ማንነቱ የማይታወቅ፣ የተቆራረጠ ሰው ፎቶም ተለጥፏል፡፡ ነገሩ ገረመኝና ለኢ.ትዮጵያ የልዑካን ቡድን አባላትም ይዤላቸው ሄድኩ፡፡ በወቅቱ ለራሴ ያነሳሁት ሃሳብ*

*“በዚህ ደሴት አንድም ኢትዮጵያዊ ይኖራል ብሎ ማሰብ አስቸጋሪ ነው፡፡ ታዲያ ይህንን ወረቀት አባዝቶ የከመረው ማን ነው?” የሚል ነበር፡፡ የዚህ ጥያቄ መልስ ምንም ይሁን ምን ነገሩ የሀገሪቱን ገጽታ የሚያበላሽ፣ በውሸት የተሞላ ሀሰተኛ ሰነድ በመሆኑ ወረቀቱ ወደተቀመጠበት ሥፍራ ተመለስኩና ወረቀቱን በሙሉ ሰብስቤ ቦርሳዬ ውስጥ ከትቼ ወደ አዳራሹ ተመለስኩ፡፡*

*የሚገርመው ነገር በዚያ ስብሰባ ላይ የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን መሪ፣ በቀኝ በኩል በኤርትራ ልዑካን መሪ፣ በግራ በኩል በወ/ሮ አና ጎሜዝ ተከበው መሀል ላይ እንዲቀመጡ ነበር የተደረገው፡፡ ነገሩ አጣብቂኝ ነበር፡፡ ለመመካከርም አይመችም፡፡ …ከጥቂት ቆይታ በኋላ ስብሰባው ተጀመረ፡፡ በዕለቱ ከነበሩት አጀንዳዎች አንዱ የአፍሪካን የምርጫና የፖለቲካ ሁኔታ በተመለከተ ስለነበር፣ ኤርትራ ወይም ወ/ሮ አና ጎሜዝ አንዳች ነገር ሊናገሩ እንደሚችሉ ገምተናል፡፡ እንደገመትነውም ወ/ሮ አና እንዲናገሩ እድል ሲሰጣቸው ‘…በኢትዮጵያ ያለው አምባገነን መንግስት ነው፡፡ ሰዎችን ያስራል፣ ይገድላል… በሀገሪቱ የመጀመሪያዋ ሴት የፓርቲ መሪ እና በ2005 ምርጫ አሸንፋ የፓርላማ አባል የነበረችውን ብርቱካን ሚደቅሳን የፓርላማ መቀመጫዋን ቀምቶ እስር ቤት ወርውሯታል…’ በማለት ተባዝቶ የተቀመጠው ወረቀት ላይ የተጻፈውን መረጃ አንድ በአንድ እየጠቀሰች ተናገረች፡፡ የወ/ሮ አና ጎሜዝን ንግግር ካደመጥኩ በኋላ ያንን ወረቀት አባዝቶ ማን እንዳሰራጨው ለመገመት አላዳገተኝም፡፡*

*የሚገርመው ነገር ያንን ወረቀት አዘጋጅተው ለወ/ሮ አና ጎሜዝ የሰጧቸው ሰዎች (ኢትዮጵያውያን ተቃዋሚዎች መሆናቸው ጥርጥር የለውም) በጣም አሳስተዋቸዋል፡፡ ምክንያቱም ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ በምርጫ 1997 ዓ.ም (እ.ኤ.አ 2005) አልተወዳደሩም፡፡ ስላልተዋዳደሩ የፓርላማ መቀመጫ አልነበራቸው፡፡ በምርጫው ወቅት የቅንጅት አባልም አልነበሩም፡፡ እንኳን የቅንጅት የእናት ፓርቲያቸው የቀስተ ደመና ፓርቲ አባልም አልነበሩም። ካልተሳሳተኩ እርሳቸው የቀሰተ ደመና ፓርቲ አባል የሆኑት ምርጫው ካለቀ በኋላ በነሃሴ 1997 ዓ/ም እነደነበረ አስታውሳለሁ።*

*የኢትዮጵያ የልዑካን ቡድን መሪ ይህን ሁሉ መረጃ ከያዙ በኋላ በሰጡት ምላሽ ወ/ሮ አና ጎሜዝ በተሳሳተ መረጃ ላይ ተመስርተው ኢትዮጵያን እየወነጀሉና ጉባኤውን እያሳሳቱ*

መሆኑን አስረዱ። በተለይ የአካፓ ሃገራትን ታዳጊ የዴሞክራሲ ሂደት ማገዝና መደገፍ ሲገባቸው ፍፁመ ውሸት የሆነ መረጃ በማቅረብ የሃገር ስም ማጥፋታቸው ትክክል ባለመሆኑ የአካፓ ሃገራት የፓርላማ አባላት፣ በአባላቸው በኢትዮጵያ ላይ እየተካሄደ ያለውን ተራ ውንጀላ በተናጥል ስብሰባ መርምረው አቋም መያዝ እነደሚኖርባቸው አሳሰቡ። ከስብሰባው በኋላ ወ/ሮ አና ጎሜዝን አግኝቻቸው ያቀረቡት ሃሳብ የተሳሳተ መሆኑን ስነግራቸው 'እኔ ምን ላድርግ' ማለታቸውን አስታውሳለሁ።" ነበር ያሉት አቶ አብዱራህማን።

እንግዲህ የዚህ አይነት ፀያፍ ተግባር ፈፃሚዋ አና ጎሜዝ የመሩት የአውሮፓ ህብረተ የምርጫ ታዛቢ ቡድን ነው የምርጫውን ውጤት በተመለከተ ተገቢ ያለሆነ ሪፖርት ያወጣው። በ97ቱ ምርጫ ላይ አና ጎሜዝ የሚመሩት "የምርጫ ታዛቢ" ተብዬ ቡድን ያወጣው ገለልተኝነት የጎደለው ሃሰተኛ ሪፖርት ምርጫውን ተከትሎ ለተቀሰቀሰው ሁከት የራሱ አስተዋፅኦ ነበረው። በዚህ ሁከት መናጆ ሆነው ህይወታቸው ለጠፋና አካላቸው ለጎደለ ዜጎችና ሰላም በማስከበር ስራ ላይ ተሰማርተው የነበሩ የፖሊስ ሰራዊት አባላት፣ ለወደመ የህዝብ፣ የመንግስትና የግል ንብረት፣ አጠቃላይ ሁኔታው በሃገሪቱ ዴሞክራሲ ላይ ለጣለው ጠባሳ በአና ጎሜዝ የሚመራው የምርጫ ታዛቢ ቡድንና የአውሮፓ ህብረት የታሪክ ተወቃሾች ናቸው።

የሚገረመው በአጠቃላይ በ1997 በተካሄደው ሃገራዊ ምርጫ ላይ የተዛባ ሪፖርት ያወጣው በአና ጎሜዝ የሚመራው የምርጫ ታዛቢ ቡድን በመላው ሃገሪቱ ከሚገኙ 90 ሺህ የምርጫ ጣቢያዎች የታዘበው 250 ያህሉን ብቻ መሆኑን ነው። እእነዚህ አዲስ አበባን ጨምሮ በዋና ዋና ከተሞች የነበሩ የምርጫ ጣቢያዎች ናቸው። በእነዚህ አካባቢዎች ደግሞ ተቃዋሚዎች ከፍተኛ ድምፅ አግኝተው በክልልና በፌደራል የህዝብ ተወካዮቸ ምክር ቤቶች ውስጥ ለመወከለ በቅተው ነበር። ይህ እውነታ የአውሮፓ ህብረት በአጠቃላይ የሃገሪቱ ምርጫ ላይ "ትክክል ነው ወይም አይደለም" የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሰ የማይችል እንደነበረ ያሳየናል። ማደረግ የነበረበት በታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫው ሂደት ምን ይመስል እንደነበረ ምስክርነት መስጠት ብቻ ነበር፤ ይህን አላደረገም።

**ይቀጥላል**